ዴሞክራሲያ

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን

ዴሞ ቅጽ 34 ቁጥር 3 ኅዳር 2001 ዓ.ም.

# ሁሉም ድርሻውን ካልተወጣ፤ የሀገር ነፃነት አይመጣ

የታሪክ ውጣ ውረድ ጉዞ ሕዝብን ደግሞ ደጋግሞ መፈተታኑ የሚጠበቅ እንደመሆኑ መጠን ሲያደናቅፍ ደፋ የሚባል ከሆነ ፤ ሲጎረብጥ ወይኔና ወገቤን ማለቱ ካየለ፤ አቃቅማው ከልክ በላይ ሲያም ተስፋ የሚያስቆርጥ ከሆነ ተከታዩ ክስተት ለሀገር የሚበጅ አይሆንም ቢባል አከራካሪ አይሆንም:: መራራውን ተጎንጭቶ፤ ለኮሶው እሬትን ጠጥቶ መፍትሔ መሻት ሲገባ ልጄ ይቅርብኝ ምጡ ለምኔ ከመጣ መጨረሻችን ሊያምር አይችልም:: ከአርበኝነት ባንዳነት፤ ለሀገር ከመሰዋት ተጎንብሶ መበርከት ከተመረጠ በጫንቃችን ላይ የተጫነው ቀንበር መውረጃው ጊዜ ገና ገና ይሆናል:: ለዚህም ነው ለሀገር ነፃነት፤ ለሕዝብ መብት መከበር ሁሉም ዜጋ ድርሻውን መክፈል፤ ሸክሙን መሸከም፤ መከራውን መቀበልና መስዋዕትነቱንም መክፈል ያለበት::

አንዳንድ የታሪክ ማፈሪያዎች የሀገር ሚዛ ና ክብደት፤ የሀገር ትርጉምና ምንነት እየጠፋቸው አንዴም ሀገርን ሲክዱ፤ በሌላ ጊዜም ኢትዮጵያዊነታቸውን ለድርድር ሲያቀርቡ፤ የፈጠራ ታሪክ ፅፈው ወይም አስተጋብተው የሀገርን ማንነት ሲበርዙ፤ በወያኔያዊ ዘረኝነት ሲበከሉ፤ ባንዳነትን ሲመርጡ ማየት መታዘብ ብንገደድም ሀገር ከሁሉም በላይ ማንነታችንና ሰብዕናችንን ገላጭ፤ መኖሪያችን፥ መቀበሪያችን፥ ቅዱስ ምድራችን መሆኗን መሰረዝ የሚችል ማንም ኃይል አለመኖሩም ግልፅ ነው:: ኢትዮጵያዊነትን የሚቀማን ሆነ የሚያደራድረን ማንም ኃይል የለም:: እንደ ጠባቦቹ፤ የፈለግነው ከሆነልን ኢትዮጵያዊ፤ ተቀባይ ካጣን ደግሞ ተገንጥለን ባዕድ ነን የሚል መርህ ግብር ልናወጣ ቀርቶ ልናስበውም የምንችለው ጉዳይ አልነበረም፤ አይደለም:: ይህ ወያኔያዊ ምርጫ ፀረ ኢትዮጵያ በመሆኑ ገና ሲቀነቀን የተቃወምነው ከመሆኑ ሌላ ኢትዮጵያን የሚክድ አማራጭ፤ ኢትዮጵያን ለቅርጫ የሚዳርግ መፍትሔ፤ ሀገራችንን ለባዕድ ተገዢ የሚያደርግ ፖለቲካ መቸም ቢሆን መቼ የምንቀበለው ሆኖ አያውቅም:: ሀገሩን የካደ ሰብዕናውን የሰረዘ ነውና ኢትዮጵያዊነቱን ገና ከመነሻው የካደው ጋር ስለ ግዴታና የዜጋ ድርሻ መወያየቱም ከባድ ይሆናል:: ሰው ሀገሩን

በአፉም በድርጊቱም ይክዳል፡፡ ኢትዮጵያዊ አይደለንም ብለው አፍ አውጥተው የሚክዱት እንዳሉ ሆነው ሀገር ወዳድ ነን፣ ኢትዮጵያዊ ነን፣ ለሀገራችን ተቆርቋሪና ሟች ነን እያሉ ለሆዳቸው ያደሩት አደገኛ ከሀዲዎች ደግሞ ጥቂቶች አይደሉም፡፡ ሆዳም እምብርትም፣ ሀገርም የለውምናም ኢትዮጵያን ለካዱት ወያኔዎች ያደሩት ሆዳሞች ሀገራቸው በተጨባጭ ኢትዮጵያ ሳትሆን አይጠግቤ ከርሳቸው ነው ፡፡

ሀገሩን ከልቡ የሚወደው ዜጋ ግን ሀገሩን የማዳን የመጠበቅ ግዴታ አለበትና ይህን ግዳጅ አልቀበልም ለማለት ህሊናው አይፈቅድለትም፡፡ ከሀገር በፊትና በላይ ምንም ሆነ ማንም የለምና ሀገሩን አስቀድሞ ለሀገሩ ደህንነት ይቆማል፡፡ ሕይወቱና ክብሩ ከሀገር ክብርና ህልውና ጋር የተቆራኙ ናቸው፡፡ ከራስ በላይ ነፋስ ሳይሆን ከሀገር በላይ ነፋስ ነው እምነቱ፡፡ በመሆኑም ሀገር ወዳዱ ዜጋ ለሀገሩ ዘብ ይቆማል፣ ሁሉም ድርሻውን ይወጣል፣ ግዳጁን ይፈፅማል፡፡ ሁሉም ሲባል ምልዓተ ህዝቡ አለመሆኑ ደግሞ የታወቀ ጉዳይ ነው፡፡ አርበኛ በበቀለበት ባንዳውም አለሁ አለሁ ማለቱ አይቀርም፡፡ የዘመናዊ ባንዶች ምሳሌዎች እነ ኃይለ ሥላሴ ጉግሳና አስረሱ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ ስንዴና እንክርዳዱ፣ ሰይጣኑና መልዓኩ፣ ክፉና ደጉ፣ ከሀዲውና ሀገር ወዳዱ፣ ተለጣፊውና ፀረ ወያኔው በታሪክ ክስተት ተቆራኝተውና አንዱ ሌላውን አጃቢ ሆነው መከሰታቸው የግድ ሆኗል፡፡ ለዚህም ነው ዛሬ ፀረ ወያኔ ጀግኖች ተይዘው ደብዛቸው ሲጠፋና መስዋዕትነትን ሲከፍሉ በዚያው ልክ ባይሆንም የሀገር ማፈሪያዎች ለወያኔ ተንበርክከውና ለሆዳቸው አድረው ሀገርን ሲያደሙ ማየት የተገደድነው፡፡ ወርቅ ረክሶ መዳብ የነገሰበት ዘመን የመጣ መስሎ ሲጋረጠብንም አንዳንዴ ለምፀት የምንዳረገው በዚሁ ነው፡፡ ሀገርን እማዬ ያላት ሁሉ ጡት ነካሽ ላለመሆኑ ማረጋገጥ የግድ ነው፡፡ የሞተልሽ ሳይሆን የገደለሽ በላ የተባለው ተደጋግሞብናልና እማዬ ኢትዮጵያ ያለው ሁሉ እውነትም ለኢትዮጵያ ይሞትላታል ብለን በጭፍኑ መደምደም ከጅልነት ቢያስፈርጀን መቃወም አንችልም፡፡ ወርቅ በእሳት ይፈተናል እንደተባለው ሀገር ወዳድ በተግባር መፈተን አለበት፡፡ ለባለሥልጣንና ለሆዱ ደፋ ቀና ያለው ሁሉ ፈጣን ምላሱን በኢትዮጵያዊነት ልፈፋ ቃኝቶ ቢያጮህ እውን ኢትዮጵያዊ፣ ሐቀኛ ታጋይ፣ ቆራጥ ሀገር ወዳድ ብለን ልንወስደው ልንወስዳት ከተነሳን ስህተታችን ከባድና ሀገርንም ጎጂ ይሆናል፡፡

የወያኔ መንጋ ሥልጣን ላይ በወጣበት ዋዜማ አረመኔው ደርግ ከተወገደ የከፋ ሊመጣ መቻሉን አንቀበልም ብሎ የተሞኘው ዜጋ ቁጥር ትንሽ አልነበረም፡፡ የኢሕአፓ ጠንቀቅ እንበል ጩኸት ከተወሰኑ ሀገር ወዳዶች ውጪ ሰሚ አጥቶ፣ ወያኔና አጋሮቹ ኢሕአፓንም ወግተው ወደ አዲስ አበባ ሲገሰግሱ እሰየው ያለው ዜጋ ወይም ጠባቦቹ ሀገር ወዳዶችን ጨፍጭፈው ወደ ሥልጣን መሮጣቸውን አላይም ያለው ክፍል ውሎ አድሮ እባብን በጉያው ማስገባቱን ማወቅ መገደዱ አልቀረም፡፡ ግን ወርቅ ጊዜ አልፎ ለወያኔ መደላደያ ዋለ ፡፡ ፀረ ኢትዮጵያ የሆነውን የወያኔን መንጋ ልጆቼ ያሉ መድረኩን አጣበውና የጠባቦች ጠበቃዎች ጩኸት ሐቅን አላሰማ ብሎ ሀገር ለከፋ አደጋ

*ተጋለጠች:: ለወያኔ ገንዘባቸውን፣ ጉልበታቸውንና ልባቸውንም አሳልፈው የሰጡ ግና ሀገር ወዳድ ነን ያሉ ወዶ ገባዎችና ተለጣፊዎች ኢትዮጵያን ጎዱት:: ሊደገፉ ይገባ የነበሩ የኢትዮጵያ ታጋይ ልጆች ትምክህተኛና ፀረ ሰላም ተብለው ተወገዙ፣ በጦረኝነትም ተብጠለጠሉ:: ሀገር አጥፊ የክፍፍልን መርዝ ወያኔ ሲረጭም÷ ነቃን አወቅን ያሉት ሳይቀሩ በጎጥ በብሔረሰብ መደራጀትን ብልጥነት ብለው በመቀበል በኢትዮጵያዊነት ላይ በደል ወደዱም ጠሉም በገቢር ፈፀሙ:: ይህ ሁሉ መለስ ብለን ልናየውና ልንቀበለውም የሚገባ ሀቅ ነው::*

*ይህን ሁሉ የምንለው ያ ተሳሳተ ያ ደግሞ ከስህተት ነፃ ሆኖ ባጀ በሚል አንዱን ለማውገዝ ሌላውን ለማሞገስ ሳይሆን ካለፈው ስህተት መማር ካልተቻለ ስህተትን መድገም አይቀሬ መሆኑን ለማሳሰብ ነው:: ታሪኩን የረሳ ስህተቱን ይደግማል፣ ሐቅን የዘነጋ ሀሰትንም ያቅፋል ነውና ነቃ ብለን፣ ውዥንብርን አርቀን፣ ከሀገር የነገ ዕጣ አንፃር ወዳጅና ጠላትን ለይተን መገኘት በጣም ወሳኝ ነው:: ወያኔ ወደ ሥልጣን ሲጠጋ ነቅተን አውቀን በነበረ ኑሮ፣ ምን ሊመጣ እንደሚችል ለመግለጽ ይጮህ የነበረውን ኡኡታ ጆሮ ሰጥተን ሰምተን በነበረ እባቡን በእንጭጩ መቅጨት በቻልን ነበር:: ገና በሥልጣን ሳይደላደልም፣ ለፀረ አማራ ልፈፋው ጆሮ ባይሰጥ ኖሮ፣ በሀገር አጥፊው ጉዞ አጃቢ ባያገኝ ኖሮ፣ ተለጣፊ ባይቀፈቀፍለት ኖሮ ምናልባትም መደላደል በተሳነው ነበር...ወዘተ፣...ወዘተ:: ነበር ነበር ነውና ከትምህርታዊነቱ ባሻገር ጠቀሜታው ምፀትን እጮኛ ማድረግና በፀፀት መንተክተክን ማስከተል ብቻ ነው:: ትምህርት ግን ከተገበየ በተለይ መስዋዕትነት የተከፈለበት ተመክሮ ፍሬው የሚያጠግብ ይሆናል:: ለዚህም ነው ለምሳሌ የግንቦት ሰኔ 1997 በደም የተገበየን ተመክሮ ዛሬ ከአፈር ደባልቆ በ2002ቱ የወያኔ የምርጫ ጨዋታ ለመካፈል ሽር ጉድ ማለት መጀመሩ ከስህተት አልፎ በሕዝብ ላይ መሳለቅ ሆኖ የሚገመተው:: በ1997ቱ ምርጫ ሕዝብና ተቃዋሚ ድርጅቶች ያደረጉት ተጋድሎ እንዳለ ሆኖ የተፈፀሙ ስህተቶች ለዚያን ወቅት ሽንፈት ማብቃታቸው ደግሞ የታየ ነው:: ለምንና እንዴት ብሎ መገምገም ሲያንስ ነው:: የግድ ነው ማለት እንችላለን:: በመሰረቱ የመጀመሪያውና ዋነኛው ትምህርት ነፃ ምርጫ በወያኔ አገዛዝ ስር ዘበት መሆኑን ማወቅን ያመለክታል:: ከ200 በላይ የዜጎች የሕይወት ዋጋ በአዲስ አበባ ከፍለውና ለፌዴራሎችና ነፍሰ ገዳዮች ሰለባ ሆነው የሰጡን መልዕክት ይህ ነው:: በየማጎሪያውና እስር ቤቱ ከዚያን ጊዜ በፊትም ሆነ በኋላ ገብተው እየማቀቁ ያሉ ዜጎች ጩኸታቸው ይኸው ነው:: ለዚህም ነው በመጪው የወያኔ ምርጫ ይህን አረመኔ ቡድን ለማጀብና ሽፋን ለመስጠት የተዘጋጁ ሁሉ በተጨባጭ ሰልፋቸው ከሕዝብ ጎራ ሊሆን የማይችለው:: እኒህ ክፍሎች የዜግነት ግዳጃቸውን ተፃረው ፈለጉም አልፈለጉም ለወያኔ አድረዋል ብንል ትክክል ይሆናል::*

*የቀለም ትምህርት ወይም የባዕዳን የትምህርት ተቋሞች ሽልማቶች አንድን ዜጋ ከሀገርና ከትግል አንፃር አዋቂ አያደርጉም:: ይህ ሀቅ ባልነበረማ ዛሬ የሕዝብን መከራ ዋና አራማጅ የሆኑ እነ እገሌና እንቶኔ ፕሮፌሰርና ዶክተር ባልተባሉ ነበር:: ለሀገር አዋቂ የሀገርና የሕዝብን ጥቅም አስቀድሞ*

የሚገኘውና ለማንም ባዕድ ተገዢ ሆኖ ሀገርን የማይጎዳው ነው:: ዛሬ በአዋቂነትና ስልጡንነት ሽፋን፣ ራሳቸውን “ልሂቅ” አዋቂ ብለው፣ ለወያኔ ማደርን በሰበብ አስባቡ በቀጥታና በሽፍንፍን የሚያቀነቅኑ አዋቂዎች ሳይሆኑ የፖለቲካ ጅሎች--መሀይሞች ናቸው:: ሐቅን አላይ ብለው ሀሰትን ስለሚያቅፉ፣ ማወቅ የሚገባቸው ሆኖ ሳለ አለማወቅን መወናበድን ስለሚመርጡ ማለት ነው:: አሊያም ሆዳቸውንና የግል ጥቅማቸውን በማስቀደም ሀገራቸውን በተጨባጭ ስለሚክዱና ለጠላቷ በሎሌነት ስለሚያድሩ ነው:: ዛሬ ለወያኔ ያደሩት ሁሉ ማለትም ተለጣፊ ሆነው ሕዝብን የሚበድሉት ሁሉ የዜግነት ሚናቸውን የሰረዙና በዚያውም ኢትዮጵያዊ የሚያደርጋቸውን ፀጋና መለያ ከትቢያ የደባለቁ ናቸው:: ዛሬ ባይሆን ነገ ታሪክም የሚጠይቃቸው መሆኑ ስውር አይደለም:: ሕዝብ መሀሪ ነውና የ ስሐው ጎዳና ዝግ ባለመሆኑ ዛሬም ቢሆን ግን ሰልፋቸውን በማስተካከል የዜግነት ግዳጃቸውን ሊወጡ ይችላሉ:: ሀገርን ከጥፋት የማዳኑ ግዳጅ የተወሰኑ ዜጎች ወይም ድርጅቶች ብቻ ሳይሆን የብዙኀኑ ሀገር ወዳድ ዜጋ ኃላፊነት ነው:: ሁሉም ዘብ ይቁም ለሀገሩ ያሉት ያለፉት ጀግኖች መልዕክታቸው ዛሬ ከመቸውም በበለጠ ውቅታዊ ነው:: በዚህም በዚያም በኢትዮጵያ ላይ የተዘረጋው የጥፋት ወጥመድ በቀላሉ ሊታይ የሚችል አይደለም:: የመለስ ቡድን የውድቀት ጊዜው መቃረቡን አልሳተውምና በአጥፍቶ መፈርጠጥ መርህ መሠረት እየሰራ ነው:: ሀገሪቷን ለጥፋትና ለባሱ አጥፊዎች ዳርጎ፣ ሀገር ወዳድ ኃይሎችን አደባይቶ፣ ሀገሪቷን ጠባቂና ተንከባካቢ አሳጥቶና ለዳግማዊ ሶማሊያነት አሳልፎ ሰጥቶ ሊሄድ ባቀደው መሰረት እየሰራ ነው:: የዚህ አረመኔ አገዛዝ ቁንጮዎች ለኢትዮጵያ ያላቸው ጥላቻ መረን የለቀቀና የጠላት ነው:: ለኢትዮጵያ ቀናና ደጉን ያስባሉ ብሎ ራስን ማሞኘት በሀገር ላይ በደልን መፈፀም ነው:: የቁርጥ ቀን እስኪመጣ የወያኔ አገዛዝ ኢትዮጵያን እየበዘበዘና ወርቋን በመዳብ እየቀየረ ለመቀጠል ይጥራል--መውደቂያው እስኪመጣ:: ውድቀቱንም በይሁን የሚቀበል ሳይሆን ይህን የሚጠላውን ሕዝብና የሚጠላትን ሀገር አጥፍቶ ለመጥፋት የሚያሴር ነው:: በዚህም በዚያም የሚከፍተው ጦርነት መዘዙ ለሕዝብ ነው:: እያራገበ ያለው የርስ በርስ ጥላቻና ግጭት ለሀገራችን ጠንቅ ነው:: ያስፋፋው ድህነትና መከራ ሕዝብን አሽመድማጅ ነው:: ሀገሪቷን ለባዕዳን አሳልፎ መስጠቱም መዘዙ ብዙ ነው:: ሀገር ወዳድና ሀቀኛ ኢትዮጵያዊ ታጋዮችንም ማጥቃቱ ሀገሪቷን ተከላካይ አሳጪ ነው:: ለተለጣፊ ሀገሪቷን አሳልፎ መስጠቱ፣ ለሆዳሞች መድረኩን ማመቻቸቱ ሀገርን ጎጂ ነው:: ወጥመዱ በስፋት ተዘርግቷል:: መጪው የወያኔ ምርጫም ቢሆን አንደኛው ወጥመድ ሲሆን በዚሁ ሊያዙ እየተብከነከኑ ያሉት ደግሞ ሕዝብን አደናጋሪ መሆናቸው ከወዲሁ የሚታይ ነው::

እያንዳንዱ ዜጋ ለሀገሩ ዘብ መቆም አለበት ሲባል ሚናውን ለይቶ ግዳጁን መወጣት እንዳለበት ጠቋሚ ነው:: ሁሉም የሚሸከመው ክብደቱ አንድ ባይሆንም ሀገርን የማዳኑ ግዳጅ ለሌላ ትውልድ የሚለጋ ሊሆን አይችልምና ያለፈው ትውልድ በታሪክ ወረቀት ላይ የበኩሉን ምዕራፎች ፅፎ እንዳለፈው ሁሉ ይኸኛውም የራሱን ገድልና ትረካ መዝግቦ ማለፉ የግድ ነው:: በዚህም መሠረት በግንባር ቀደም ደረጃ በሕዝብ ደምና ላብ ክፍያ የተማረው ክፍል--በደፈናው ምሁሩ--ልዩ ኃላፊነት

አለበት፡፡ ያለፈው የተማረ ትውልድ በጣሊያን ወረራ ጊዜም ሆነ ከዚያ በኋላ ግዳጁን ተወጥቷል፡፡ ለሕዝብ ታግሎ ተሰውቷል፡፡ ዛሬ ምስጋና ቢስ የሆኑ የታሪክ ሰራዦች ያን ትውልድ በዚህ በዚያም ሊወቅሱና ሊያወግዙ ቢፍጨረጨሩም ያ ትውልድ መሬት ለአራሹ፣ ድኻው ይማር፣ ሠርቶ አደሩ መብቱ ይጠበቅ፣ ኢትዮጵያ በባዕድ አትደፈር፣ የሕዝብ እኩልነት ይረጋገጥ፣ የሴቶች መብት ይከበር፣...ወዘተ ብሎ ለስር ነቀል ለውጥ የታገለ ነው፡፡ አፋኝና ፋሺስታዊ ቡድን የሕዝብን ድል ቀምቶ በሥልጣን ሲሰየምም በነፍጥ ተደናግጦ ወይም በጥቅም ተገዝቶ ሕዝብን ሳይከዳ፣ ከመሀሉ የበቀሉትን ዘመናዊ ባንዳዎች አውግዞና ተለይቶ ባመነበት በመቀጠሉና ፀንቶ በመቆሙ ቀይ ሽብር የተባለውም አረመኔያዊ ፍጅት ትጥቁን አላስፈታውም፡፡ ዛሬ ኢትዮጵያ ህልውናዋ ለአስከፊ አደጋ ተጋልጦ ባለበት ሕዝብ ለፍቶ፣ ጥሮና ግሮ ያስተማረው ምሁር ሀገርን ለማዳን ሊታገል ይጠበቅበታል እንጂ ወገበ ለማጣ በመሆን ለሀገር ጠላት ሊጎነበስና በሀገሩና በወገኑ ላይ መርገም ሊሆን አይጠበቅም፡፡ ምሁር ሀገር ወዳድ ካልሆነ ምሁር ሊባል አይገባውምናም ነው፡፡ ስለዚህም ምሁሩ ሕዝብን በማደራጀትና በትግል በማሰለፍ፣ የፅናትም የቆራጥነትም አርአያ በመሆን አኩሪ የትግል ታሪክ መፃፍ መቻል ይገባዋል እንጂ ባይማሩ በቀረብን ብሎ ሕዝብ የሚያማርርበትን አሳፋሪ ሁኔታ መፍጠር የለበትም፡፡

የምሁሩ ልዩ ሚና እንዳለ ሆኖ ሀገሩን ሁሌም ደሙን አፍሶ የሚያድነው ሠፊው ሰርቶ አደር ሕዝብ ነው፡፡ ላባደሩና አርሶ አደሩ፣ ጥሮ ግሮ የሕይወትን ሻካራ ሞረድ አድርጎና አለስልሶ ቀኑን ሊገፋ የሚሞክረው ሚሊዮኑ ሕዝብ ማለት ነው፡፡ ይህ ሕዝብ በሀገሩ የመጀመሪያ ተጠቃሚ ባይሆንም ሀገሩን ለመከላከል ሁሌም ሕይወቱን የሚሰጥ መሆኑን ታሪክ በሚገባ የመዘገበው ነው፡፡ ዛሬም ኢትዮጵያን ሊያድናት የሚችለው ይኸው ሕዝብ ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ሚናውን ለማንም አሳልፎ በመስጠት መብቱና ሀገሩን ለማሰቀማት መመቻቸት የለበትም፡፡ እናውቅልሃለን ብለው ማለቂያ ለሌለው ምዝበራና ባርነት ሊዳርጉት የሚጥሩትን አፈ ጮሌዎች ማሳፈርና ሀገሩን ለማዳን በተቻለው ሁሉ መነሳት መታገል ይጠበቅበታል፡፡ ስንዴውን ከእንክርዳዱ በመለየት በሐቅ ከጎኑ የሚቆሙትን ከአስመሳዮቹ አበራይቶ በማወቅ ከሐቀኛ ሀገር ወዳድ ኃይሎች ጋር ሆኖ፣ ቀቢፀ ተስፋን ቀብሮ፣ ንጉሶች ቢሞገሱበትም በደሙ ያስገኛቸውን ታሪካዊ ድሎች ሁሉ በማደስ ሀገር አድን ገድልን ማካሄድ ይጠበቅበታል፡፡ የኢትዮጵያን ሕዝብ ሊንቁ የተነሱትን ሁሉ ሕዝብም አልተበላሸ ታሪክም አልዋሸ ብሎ ሊያስተምራቸው ማስፈለጉንም ጊዜው ያስረዳል፡፡

በደፈናው የሕዝብ ሀገር አድን ሚና ቢባልም በዚህ ውስጥ የላባደሩ፥ የምሁሩ፥ የወጣቱ፥...ወዘተ በሚል ሁሉም ያለውን ልዩ ሚና ስናጤን በተለይም ከሕዝቡ በቁጥር ከግማሽ በላይ የሆኑት ሴቶች ያላቸውን ወሳኝ ሚናና ድርሻ መጥቀሱ አስፈላጊ ነው፡፡ የሀገራችን ሴቶች ለሀገር ነፃነት ያደረጉት ተጋድሎ ተገቢውን ክብደት ተሰጥቶት ባይወሳም፣ ትምክህት የቃኘው ህብረተሰብ የሴቶችን ማንነት በተመለከተ አክቸልቻይ ተረቱን ቢደረድርም የኢትዮጵያ ሴቶች ሀገራቸውን ከውጭ ጠላት

ለመከላከል የከፈሉት መስዋዕትነት ከፍተኛ ነው:: በጣይቱ ብጡልና መሰል ነገሥታት ወይ ወይዛዝርት ደረጃ ሳይሆን በቤት እመቤቶች፥ በሠርቶ አደርሴቶች ነው ኢትዮጵያ ማንነቷንና ህልውነዋን ጠብቃ የቆየችው:: በመሆኑም ዛሬ ሀገሪቷን ከጥፋት ለማዳን በሚደረገው ወሳኝ ፍልሚያ የሴቶች ግንባር ቀደም ሚና ካልተረጋገጠ ሀገርን የማዳኑ ተልዕኮ ሊሟላ አይችልም:: ለዚህም ነው ሴቶች በተለይ የትግል ግዳጃቸውን ለመወጣት ከመቸውም ጊዜ በበለጠ ዝግጁ ሆነው መገኘት ያለባቸው:: ትግሉን ከድል ማድረስና ሀገራዊ ግዳጅን መወጣት፥ ከዚያም አልፎ የሥልጣን ባለቤት መሆን የሕዝብ ጉዳይ ቢሆንም ከሕዝብ አብራክ ወጥተው ለሕዝብ ጠላት ክንድና ምሰሶ የሆኑት ደግሞ ልዩ ኃላፊነት አለባቸው:: ማለትም የገዢው ክፍል ጦር ሠራዊት አባል በመሆን የሚያገለግሉ ዜጎች የወደሩትን ጠመንጃ አፈሙዙን ወደ ገዢው ክፍል በማዞር የሕዝብን ትግል ማገዝ ለሕዝብ የድርሻቸውን አስተዋፅዖ ማድረግ ይገባቸዋል ማለት ነው:: በሕዝብ ደም እያጨማለቀ ራሳቸውንም በየጦርነቱ ለሞት እያዳረገ ያለውን አገዛዝ መታዘዝ ሳይሆን በላዩ ላይ ማመፅ እንዳለባቸው ሁሉም ወታደሮች፥ ፖሊሶች፥ መኮንኖች ማወቅ አለባቸው::

ሀገርን ማዳኑ የጋራ፥ የብዙኃኑ ግዴታ ነው:: ለዚህ ግዳጅ ስምረት ሕዝብ ኃይሉን ራሱን ማደራጀት እንዳለበትም ታሪክ ያስተምራል :: ያልተደራጀ ሕዝብ በተደራጀ ጠላቱ ላይ ድልን ሊቀዳጅ አይችልም:: ይህን ሐቅ ሕዝባችን ደሙን አፍሶ ተምሮታልና ዛሬ ወደ ኋላ ወስደው የተደራጀን ጠላት በግርግር ስብስብ ግጠሙት የሚሉትን ጆሮ መስጠት አያሻም:: ሕዝብ መሪ ድርጅቱን/ድርጀቶቹን ማወቅ፥ መደገፍና ማጠናከር ያለበትም ለዚህ ነው:: የትግል መሣሪያዎቹ ናቸውና ድርጀቶቹ ዙሪያ በመሰለፍ በሀገር አድኑ ትግል መግፋት አለበት ማለት ነው:: ድርጅት ስንልም የሚታገልና የሚያታግል ለማለት እንጂ በስመ ድርጅት ራሳቸውን ሞሽረው ከትገሉም ከሕዝብም የራቁትን ለማለት ሊሆን አይችልም:: ሀገር የጋራ ናት--ምንም እንኳን ጥቂቶች ብቻ ተንደላቀው ቢኖሩባትም:: ሀገርን ማዳን የጋራ ግዴታ ነው--ማዳኑ ደግሞ ሀገርን የጋራ የሁሉ ለማድረግ ነው:: ሌላ አላማ ሊኖረው አይጠበቅም:: ኢትዮጵያን ከሰፈሩባት የጠባብ ጋኔኖች ልናላቅቅ ሕይወት የምንገብረው ለጥቂቶች መፈንጫ ሆና ትቀጥል ዘንድ ሳይሆን ዴሞክራሲ የሰፈነባት የሕዝቧ ሀገር እንድትሆን ነው::

ለሀገር አድኑ ትግል ግዳጃችንን እንወጣ!!